ራስን የማብቃት ዕቅድ ፎርማት

I. እንደ መግቢያ

የዚህ ፎርማት ዓላማ በተቋሙ ያሉ ሁሉም ፈፃሚዎች ተመሳሳይነት ባለው መልኩ በዕለት ተዕለት ተግባር አፈፃፀም ረገድ እና የወደፊት ዕድገት ፍላጎታቸውን ለማሳካት ምላሽ ሊሰጣቸው የሚችል ራስን የማብቃት ዕቅድ ለማቀድ ያሉባቸውን ክፍተቶች በመፈተሽ በራስ ጥረት፣ በቡድኑ አባላትና በሌሎች የተቋሙ ሠራተኞችና በታቀደ መልኩ በሚሰጣቸው የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ራሳቸውን የሚያበቁበትን ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ለማድረግ ነው።

ጠቀሜታውም በዕቅዱ ውስጥ መካተት ያለባቸው ጉዳዮች ሳይንጠባጠቡ እንዲታቀዱ በማድረግ የዕቅድ ዝግጅቱን ጥራት ማስጠበቅና በሚደረገው ድጋፍና ክትትል ለቡድኖቹ ተመሳሳይ ፎርማት በመከተል ግብረ መልስ ለመስጠት እንዲቻል ነው። በመሆኑም ሁሉም የተቋሙ ሰራተኞች ዕቅዳቸውን ሲያዘጋጁ ይህንን ፎርማት መከተል ይኖርባቸዋል።

II. ዕቅዱ የሚይዛቸው ዋና ዋና ጉዳዮች

1. የሽፋን ገፅ

   ዕቅዱ የሽፋን ገፅ ይኖረዋል። በሽፋን ገፁም ከዚህ በታች ያሉትን ጉዳዮች ያካትታል።

በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን

በ.....ዳይሬክቶሬት

የ 2010 በጀት ዓመት ራስን የማብቃት ዕቅድ

የዕቅዱ ባለቤት፡-.....

የስራ ድርሻ፡-.....

አሁን በያዘው የስራ መደብ የቆየበት ጊዜ፡- .....

ዕቅዱ የፀደቀበት ቀን፡- .....

2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

2. መግቢያ

አጭርና ግልፅ የሆነ መግቢያ ይኖረዋል። መግቢያው ውስጥ ዕቅዱ ያስፈለገበትን ምክንያትና ዕቅዱን ለማሳካት የምናከናውናቸውን ተግባራት የአፈፃፀም አቅጣጫ የሚያላክት ወይም የሚዳስስ ሆኖ መዘጋጀት አለበት።

3. የዕቅዱ ዓላማ

የዕቅዱ ዓላማ ግልፅ ሆኖ መቀመጥ ይኖርበታል። የምናስቀምጠው ዓላማ ከምናከናውናቸው ተግባራ ጋር ተናባቢ የሆነና በዓመቱ መጨረሻ እንደርስበታልን ብልን ወደ ካስቀመጥነው ግብ ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት።

4. የነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ

በነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ባለፈው በጀት ዓመት ሠራተኛው ከታች ከ 4.1 እስከ 4.3 ከተዘረዘሩት ዓበይት ነጥቦች አንፃር በውጤት ተኮር ምዘና፣ በዙሪያ መለስ ምዘናና በሌሎች ግምገማዎች የተነሰብትን ጉዳዮችና የተሰጠውን ግብረ መልስ መሠረት በማድረግ እንዲሁም ከሌሎች ባልደረቦቹ ጋር ውይይት በማድረግ ስለ ድክመትና ጥንካሬው መረጃ በማሰባሰብ የበሩትን ጥንካሬዎችና ክፍተቶች በአግባቡ መዳሰስ ያስፈልጋል።

ከአመለካከትና ከክህሎት ጋር የተያያዙት ክፍተቶች ከተለዩ በኋላም ለተለዩት ክፍተቶች መሠረታዊ የሆነው መንስኤ በአግባቡ መታወቅ ይኖርበታል። “በሽታውን ያላወቀ መድሃኒት አያገኝም“ እንደሚባለው ሁሉ ለክፍተቶቻችን ትክክለኛውን ምንጭ ወይም መንስኤ በአግባቡ እስካልለየን ድረስ ትክክለኛ የመፍትሄ ዕርምጃ መውሰድና ከክፍተቶቻችን መቆራረጥና አፈፃፀማችንን ማሻሻልና የወደፊት ዕጣ ፈንታችንንም ብሩህ ማድረግ ስለማንችል መንስኤውን በአግባቡ መረዳት ይኖርብናል።

በአጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታውን በአግባቡ መዳሰስ በቀጣይ በምናቅደው ዕቅድ ጥንካሬዎቹን ይዘን የምንቀጥልበትና ክፍተቶቹን በመዝጋት የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖረን ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ጉዳይ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል። እነዚህም ክፍተቶች በድርጊት መርሃ ግብር ሰንጠረዡ አሁን ያለብኝ የአመለካከት/ የክህሎት ክፍተት በሚለው ዓምድ ስር ክፍተቶቹ/ ችግሮቹ የሚፈቱበት ስልት፣ የሚፈቱበት ጊዜ፣ ችግሩን ለመፍታት የሚያስፈልገው ሃብት... ወዘተ የሚካተቱ ይሆናል።

4.1. ሠራተኛው አሁን በተመደበበት ቦታ ያለውን አፈፃፀም ከማሳደግ አንፃር

- ጥንካሬ (ያሉ ምቹ ሁኔታዎች)
- በክፍተት (በዕጥረት) የሚታዩ
- የድክመቶቹ መሠረታዊ መንስኤዎች

4.2. ሠራተኛው አሁን በተመደበበት ቦታ ከሚታሰቡ ለውጦች ጋር ራሱን ብቁ ከማድረግ አንፃር

- ጥንካሬ (ያሉ ምቹ ሁኔታዎች)
- በክፍተት (በዕጥረት) የሚታዩ
- የድክመቶቹ መሠረታዊ መንስኤዎች

4.3. ሠራተኛው የወደፊት ዕድገት ፍላጎቱን ከማሳካት አንፃር

- ጥንካሬ (ያሉ ምቹ ሁኔታዎች)
- በክፍተት (በዕጥረት) የሚታዩ
- የድክመቶቹ መሠረታዊ መንስኤዎች

5. በዓመቱ መጨረሻ የሚደረስባቸው ግቦች

በዚህ ክፍል ሠራተኛው በዓመቱ መጨረሻ ላይ ከላይ በነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ያነሳቸውን ጥንካሬዎች የበለጠ አጠናክሮ በመቀጠል እና ከአመለካከትና ከክህሎት ጋር በተያያዘ በክፍተት ያነሳቸውን ጉዳዮች በማስተካከል ከላይ በነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ከታዩት ዓብይ ጉዳዮች ማለትም በያዘው ቦታ ላይ አፈፃፀሙን ከማሳደግ፣ አሁን በሚሰራበት ቦታ ከሚመጡ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር አብሮ በመራመድ ራሱን ብቁ ከማድረግና የወደፊት የዕድገት ፍላጎቱን ከማሳካት አንፃር ግልፅና ተጨባጭ የሆኑ ግቦችን ማስቀመጥ ይኖርበታል።

ግቦችን ስናስቀምጥ ታሳቢ ልናደርገው የሚገባን ጉዳይ በስራችን ዙሪያ ያለንን ሚናና ኃላፊነት እንዲሁም የተቋሙን ፍላጎት ግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚገባን ነው። ይህም ማለት የሚቀመጡት ግቦች የሠራተኛውን ራስን የማብቃት ዕቅድ ከማሳካት በተጨማሪ የተቋሙን ራዕይ፣ ተልዕኮና ስትራቴጂክ ዕቅድ የሚያሳኩ መሆን እንደሚገባቸው ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል ማለት ነው።

6. በዓመቱ መጨረሻ የሚደረስበት ጥቅል ግብ

በዓመቱ መጨረሻ የሚደረስበት ጥቅል ግብ ከላይ ከሶሰቱ ዓበይት ጉዳዮች አንፃር በክፍተት ያነሳናቸውን ጉዳዮች አስተካክለን በዓመቱ መጨረሻ እንደርስበታለን ያልናቸውን ግቦች በጥቅሉ የሚገልፅና የራስን የማብቃት ዕቅዳችንን አቅጣጫ የሚያመላክት መሆን አለበት።

7. የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትና የሚያስፈልገኝ ድጋፍ ወይም ሃብት

7.1. ዓላማዬን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት

በዚህ ክፍል የሚቀመጡት ተግባራት ከላይ በተራ ቁጥር 4 በንዑስ ተራ ቁጥር ከ 4.1. እስከ 4.3. ላይ በዕጥረት ወይም በክፍተት ያነሳናቸውና መንስኤያቸውን ያስቀመጥናቸውን ችግሮች ለመፍታት ከእያንዳንዱ ክፍተት አንፃር የምናከናውናቸውን ተግባራት ወይም የምንወስዳቸው እርምጃዎች ናቸው። እነዚህም ተግባራት በድርጊት መርሃ ግብር ሰንጠረዡ ዓላማዬን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት በሚለው ዓምድ ስር የሚካተቱ ይሆናል።

7.2. ዓላማዬን ለማሳካት የሚያስፈልገኝ ድጋፍ **(ሃብት)**

በዚህ ክፍል እናሳካቸዋለን ብለን የያዝናቸውን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስፈልጉን የግል ራስን የማብቃት ጥረቶች (ዕርምጃዎች)፣ ከባልደረቦቻችን ልናገኛቸው የሚገቡ ድጋፎች፣ በታቀደ መልኩ ልናገኛቸው የሚገቡን ስልጠናዎች፣ ተግባራችንን ለማከናነውን የሚያስፈልገን ሃብት ወይም ግብዓቶች በዝርዝር ይቀመጣሉ። እነዚህም ጉዳዮችም በድርጊት መርሃ ግብር ሰንጠረዡ ዓላማዬን ለማሳካት የሚያስፈልገኝ ድጋፍ (ሃብት) በሚለው ዓምድ ስር የሚካተቱ ይሆናል።

8. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች

8.1. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

8.2. የመፍትሄ አቅጣጫዎች

ማስታወሻ፡-

ራስን የማብቃት ዕቅድ ክለሳ ስለሚደረግበት አግባብ

በየጊዜው የተገኘውን ለውጥና መሻሻል መገምገም ያስፈልጋል። የተገኘውን ለውጥ ወይም መሻሻል በየጊዜው መገምገም የሚያስፈልግበት ዋናው ምክንያት በተገኘው ለውጥ ወይም መሻሻል እርካታ ማምጣት ካልተቻለ የኢላማ ወይም ራስን የማብቃት አጠቃላይ አቅጣጫ ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ስለሚሆን ነው። የዒላማ ወይም ራስን የማብቃት አቅጣጫ ለውጥ ለማድረግ መነሻ የሚሆኑ ጉዳዮች በዋናነት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. አጥጋቢ ያልሆነ ለውጥ (መሻሻል) ሲኖርና በተገኘው ለውጥ እርካታ ማግኘት ሳይቻል ሲቀር፣
2. ዕቅዱን ለመፈፀም ከሚገባው በላይ ጭንቀት (ጫና) ከተፈጠረ፣
3. ዓላማውን ለማሳካት ፍላጎት ከጠፋ ወይም ከዓላማው ስኬት የሚጠበቀው ጥቅም (ውጤት) ሲለወጥ፣
4. ራስን ከማብቃት ተግባራትና አቅጣጫ ጋር የሚፃረር ከሙያ ወይም ከግል ህይወት ጋር በተያያዘ ለውጥ ሲኖር በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ እቅዱን መከለስ አስፈላጊ ይሆናል።

ተ.ቁ	አሁን ያለብኝ የአመለካከት/ የክህሎት ክፍተት	ራስን የማብቃት ዓላማዎቼ (መድረስ የምፈልገው)	ዓለማዬን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት	ዓለማዬን ለማሳካት የሚያስፈልገኝ ድጋፍ (ሃብት)	የስኬታማነት መለኪያ መስፈርት	ዓላማዎቼን ለማሳካት የተቀመጠ ቀነ ገደብ	ምርመራ

9. ራስን የማብቃት ዕቅድ የድርጊት መርሃ ግብር